Treatment Action Group

# መድኃኒት ለሚቋቋም የሳንባ ህመም የሚደረገውን ክሊኒካዊ እና በላብራቶሪ ላይ የተመሰረተ ክትትል እንዲሁም ከህክምናው ጋር ተያይዞ ሊከሰቱ የሚችሉ የጎንዮሽ ጉዳቶችን አስመልክቶ ምን ሊጠበቅ ይችላል?

*ጸሃፊ፡ ጄኔፊር ፈሪን*     *ትርጉም፡ ሊንድሲ ማኬና*     *መጋቢት* 2025

መድሃኒት የሚቋቋም የሳንባ ህመም (DR-TB) ሕክምና በጣም ውጤታማ ነው, ነገር ግን ህመሙን ለማከም ጥቅም ላይ የሚውሉ መድሃኒቶች የጎንዮሽ ጉዳቶችን ሊያስከትሉ ይችላሉ.። እነዚህን በፍጥነት ለመለየት እና ምላሽ ለመስጠት፣ የህክምና አገልግሎት ሰጪዎች እና ህክምና እየተደረገላቸው ያሉ ሰዎች የጐንዮሽ ጉዳቶቹን አስቀድመው ሊያመላክቱ የሚችሉ ማሳያዎችን መረዳት ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም  የህክምና አገልግሎት ሰጪዎች በተቻለ ፍጥነት የጐንዮሽ ጉዳቶችን ለመለየት አስፈላጊ የሆኑ ምርመራዎችን እና ክትትሎችን ሊያደርጉ ይገባል። ጊዜውን የጠበቀ ምርመራ እና ክትትል ማድረግ የህክምናውን የጐንዮሽ ጉዳቶችን አደጋ ለመቀነስ እና ሰዎች በተቻለ ፍጥነት ጤንነታቸውን መልሰው እንዲያገኙ ለማረጋገጥ ወሳኝ መንገዶች ናቸው።

ህክምና ከመጀመሩ በፊት አንዳንድ ምርመራዎች መደረግ አለባቸው። ይህ ብዙውን ጊዜ **“የመነሻ”** ምርመራ ተብሎ ይጠራል። በህክምናው ወቅት የሚከሰቱትን ለውጦች በተሻለ ለመረዳት እንዲቻል ህክምናው ከመጀመሩ በፊት ምን እየተከሰተ እንዳለ ያረጋግጣል። “**የቋሚ ክትትል/ምርመራ**” ማለት ምንም ዓይነት የህመም ስሜት ባይኖርም እንኳ መድሃኒት በሚቋቋም የሳንባ ህመም  ህክምና ወቅት ለሁሉም ሰው መደረግ ያለባቸው ምርመራዎች/ክትትሎች ማለት ነው። **“በህመም ምልክት ላይ የተመሰረተ ምርመራ**” የሚያመለክተው በህክምና ላይ ያለ ሰው የተለዩ ችግሮችን ወይም ስጋቶችን ሪፖርት ሲያደርግ የሚደረጉ ምርመራዎችን እና ግምገማዎችን ነው። እነዚህ የምርመራ አይነቶች ኢንደሚከተለው ተብራርተዋል። ሦስቱም የክትትል ምርመራዎች በብሔራዊ የሳንባ ህመም ፕሮግራም ፤ በተለይም መድኃኒት ለሚቋቋም የሳንባ ህመም በተዘጋጀው አጠቃላይ የህክምና ፓኬጅ ውስጥ የተካተቱ ስለሆኑ የህክምና ክትትሉን ለሚያገኙ ሰዎች ሁሉ ያለ ተጨማሪ ወጪ ይሰጣሉ።

ለታካሚዎች የሚደረጉት የክትትል ምርመራዎች በህክምናው ሂደቱ ውስጥ በተካተቱት መድኃኒቶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ ለብዙ መድሃኒት የሚቋቋም የሳንባ ህመም ታካሚዎች የሚመከሩ አምስት ዋና ዋና የክምና አሰጣጥ አይነቶች አሉ። የክምና አሰጣጥ ሂደቶቹ ለህክምናው የሚሰጡትን መድኃኒቶችን፤ የጐንዮሽ ጉዳቶቻቸውን እንዲሁም የክትትል ምርመራዎች እና ስልቶችን ይጋራሉ። ይህ ጽሁፍ መድኃኒት የሚቋቋም የሳንባ ህመም ያለባቸው ሰዎች ህክምና ሲጀምሩ፣ በህክምናው ወቅት እና የተወሰኑ የጐንዮሽ ጉዳቶችን ወይም ልምዶችን ሪፖርት ሲያደርጉ ሊጠብቋቸው የሚገቡትን የላብራቶሪ ምርመራዎች እና ክሊኒካዊ ምርመራዎች ዝርዝር ያቀርባል።

## መድሃኒት የሚቋቋም የሳንባ ህመም የተያዙ ሰዎች በሙሉ ህክምና ከመጀመራቸው በፊት የሚከተሉትን የመነሻ ግምገማዎች ማድረግ አለባቸው:

**1.** የአክታና የመድሃኒት ተጋላጭነት ምርመራ። የመድሃኒት ተጋላጭነት ምርመራው ቢያንስ ሪፋምፒሲን እና ፍሎሮኪኖሎኖስ የሚባሉትን የመድሃኒት አይነቶች የመቋቋም ምርመራን ማካተት አለበት። ቢቻል ምርመራው በህክምናው ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ሁሉም መድኃኒቶችን በተመለከተ የታካሚውን የመቋቋም ችሎታ እንዲመረምር ይጠበቃል።

**2.** የደረት የጨረር ምርመራ ( የደረት X-ray)

**3.** የሁሉም የሰውነት ሥርዓቶች አካላዊ ምርመራ። ይህ ምርመራ ክብደትን፣ ቁመትን፣ የማየት ችሎታን እንዲሁም በእጆቹና በእግሮቹ ውስጥ ያሉትን የነርቮች አሠራር መገምገምንም ይጨምራል

**4.** የልብን የኤሌክትሪክ ሥርዓት ለመፈተሽ የሚደረግ የኤሌክትሮካርዲዮግራም (ECG) ምርመራ

**5.** የተሟላ የደም ቆጠራ፣ የጉበት ሥራን፣ የኩላሊት ሥራን እና የፖታስየም መጠን ለመለካት የሚያስችሉ የደም ምርመራዎች

**6.**የኤች አይ ቪ ምርምራ

**7.** የእርግዝና ምርመራ፤ እና

**8.** የአዕምሮ ጤንነት ክትትል፣ የህክምና ክትትል ተግዳሮቶች እና የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ አስፈላጊነትን በተመለከተ የሚደረግ ምዘና

መድኃኒት በሚቋቋም የሳንባ ህመም (DR-TB) የተያዙ ሰዎች በህክምና ሂደቱ ውቅት ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ የጤና ባለሞያ እንዲጎበኙ ይጠበቃል። በጉብኝቱ ወቅት የጤና ባለሞያው ስለ ማንኛውም የቲቢ ምልክቶች (ሳል፣ ትኩሳት፣ ክብደት መቀነስ፣ የሌሊት ላብ፣ የመተንፈስ ችግር) መጠየቅ አለበት። በተጨማሪም የቲቢ በሽታ ያለበት ሰው ላይ ሊታዩ የሚችሉ የህክምናውን የጐንዮሽ ጉዳቶችን ሊያመለክቱ ስለሚችሉ አዳዲስ ምልክቶች መጠየቅ አለበት። እነዚህ ምልክቶች ማቅለሽለሽ፣ ተቅማጥ፣ የቆዳ ቀለም መቀየር፣ የዓይን ቀለም መቀየር፣ የዕይታ መቀየር፣ የትንፋሽ እጥረት፣ የደረት ሕመም፣ የልብ ምት፣ ራስ ምታት፣ ማቅለሽለሽ፣ ሽፍታ፣ የእጆች ወይም የእግሮች መቃጠል፤ ቅዠት፤ ማዘን፣ የተለመዱ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ ፍላጐት ማጣት፣ እንቅልፍ ማጣት፣ መጨነቅ ወይም የአስተሳሰብ ለውጥ ናቸው።

**የተያዙ ሰዎች በሙሉ በህክምናው ወቅት የሚከተሉትን መደበኛ ክትትሎች ማድረግ አለባቸው( እነዚህም ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ 1 ላይ ተጠቃለዋል)**

**1.** ወርሃዊ የአክታ ምርመራ

**2.** የሁሉም የሰውነት ሥርዓቶች አካላዊ ምርመራ። ይህ ምርመራ ክብደትን፣ ቁመትን፣ የማየት ችሎታን እንዲሁም በእጆቹና በእግሮቹ ውስጥ ያሉትን የነርቮች አሠራር መገምገምንም ይጨምራል

**3.** የልብን የኤሌክትሪክ ሥርዓት ለመመርመር የሚደረግ የሌክትሮካርዲዮግራም( ECG) ምርመራ (ይህም በየ 4-8 ሳምንታት ጊዜ ውስጥ ይደጋገማል)

**4.** የደም ቆጠራ ለማካሄድ የሚደረጉ የደም ምርመራዎች( linezolid እየወሰዱ ከሆነ በእየወሩ) እና የጉበት ምርመራ (pretomanid ወይም pyrazinamide እየወሰዱ ከሆነ በእየወሩ)

**5.** የአዕምሮ ጤና ችግሮችን አስመልክቶ የሚደረጉ ክትትሎች፤ እና

**6.** የህክምና ክትትል ተግዳሮቶችን ለመለየት እና ለማስተካከል የሚደረጉ ክትትሎች

ሰንጠረዠ **1.** የስድስት ወር የክትትል መርሃ ግብር

| የምርመራ ዓይነት | ከመጀመራችን በፊት | ወር1 | ወር 2 | ወር 3 | ወር 4 | ወር 5 | ወር 6 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የአክታ ምርመራ | X | X | X | X | X | X | X |
| የደረት ራጅ ምርመራ | X | | | | | | |
| በህክምናው ወቅት የተከሰቱ አዳዲስ ምልክቶችን ወይም ችግሮችን መገምገም | | X | X | X | X | X | X |
| የአካላዊ ምርመራ | X | X | X | X | X | X | X |
| የልብ ምርመራ | X | X | | X | | | |
| Linezolid በሚወስዱበት ጊዜ የደም ህዋስ ቁጥርን ለመቈጣጠር የሚደረግ የደም ምርመራ | X | X | X | X | X | X | X |
| pretomanid ወይም pyrazinamide በሚወስዱበት ጊዜ የጉበት ሥራን ለመቈጣጠር የሚደረግ የደም ምርመራ። | X | X | X | X | X | X | X |
| የኤች አይ ቪ ምርምራ | X | | | | | | |
| የእርግዝና ምርመራ፤ | X | | | | | | |
| የአዕምሮ ጤና ክትትል | X | X | X | X | X | X | X |
| ማያቋርጥ ድጋፍ ለመስጠት መከታትል | X | | | | | | |
| በlinezolid በሚወስዱበት ጊዜ የሚደረግ የዕይታ ምርመራ | X | X | X | X | X | X | X |
| Linezolid በሚወስዱበት ጊዜ የነርቭ ችግር ምርመራ | X | X | X | X | X | X | X |

* የጉበት በሽታ ያለባቸው ወይም የአልኮል ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎች ፕሪቶማኒድ በሚወስዱበት ጊዜ በየወሩ የጉበት ምርመራ ማድረግ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ሌሎች ሰዎች ፕሪቶማኒድ የሚወስዱ ቢሆንም እንኳን ምርመራውን ማድረግ አይጠበቅባቸውም።

ማንኛውም የህመም ምልክት ያጋጠማቸው ሰዎች ለሚረዳቸው የጤና ባለሙያ ምልክቱን ማሳወቅ አለባቸው። ይህን ሲያደርጉ ከምልክቶቹ ጋር የተያያዘ የሰውነት ሥርዓት ጥልቅ ምርመራ እንደሚደረግላቸው መጠበቅ ይኖርባቸዋል። **ከአካል ምርመራው በተጨማሪ የሚከተሉትን ምልክቶች ለሚያሳዩ ሰዎች የሚከተሉት የላብራቶሪ ምርመራዎች/ግምገማዎች ሊደረጉ ይገባል፤**

**ማቅለሽለሽ/ ማስታወክ፣ የቆዳ ወይም የዓይን ቀለም ለውጥ: ለጉበት ምርመራዎች የደም ናሙና**

**ሽፍታ: የቆዳ፣ የዓይን እና የአፍ ሙሉ ምርመራ**

**የደረት ሕመም፣ ማዞር፣ ራስን መሳት፤ የትንፋሽ እጥረት: የልብ ኤሌክትሪክ ሥርዓትን ለመፈተሽ የልብ ምርመራ፣ የፖታሲየም መጠን ለመፈተሽ የሚደረግ የደም ናሙና**

**የድካም ስሜት፣ የትንፋሽ እጥረት፣ የቀለም መቀየር፣ በቀላሉ የሚከሰት ቍስል: የደም ናሙና ለሙሉ የደም ህዋስ መጠን ምርመራ**

**በእጆች/በእግሮች ላይ የመደንዘዝ/የማቃጠል ስሜት: ሙሉ የነርቭ ምርመራ፣ በእጆችና በእግሮች ላይ የሚከሰተውን ቅጽበታዊ እንቅስቃሴ እና ስሜትን ጨምሮ።**

**የእይታ ለውጦች: ሙሉ የዓይን ምርመራ የእይታ ትክክለኛነትን ጨምሮ፣ የቀለም መለየትን እና ጥልቅ የዓይን ምርመራን ጨምሮ ሙሉ የዓይን ምርመራ ( የዓይን ጀርባን ማየት የሚያስችል ብርሃንን/ophthalmoscopy በመጠቀም የሚደረግ)።**

በመደበኛ ክትትል ወይም በምልክቶች ላይ የተመሰረቱ ግምገማዎች ማንኛውንም የጐንዮሽ ጉዳት የሚያሳዩ ከሆነ የጤና ባለሞያው በህክምናው አሰጣጥ ሂደት ላይ ለውጦችን ያደርጋል። ይህም ችግሮቹን ያስከትላል ተብሎ የተጠረጠረውን መድኃኒት መጠን መቀነስ፣ ችግሮቹን ያስከትላል ተብሎ የተጠረጠረውን መድኃኒት ማቆም ወይም ህክምናውን ሙሉ በሙሉ ማቆም ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም የጤና ባለሞያዎቹ ምልክቶችን ለመቀነስ ሊረዱ የሚችሉ አዳዲስ መድኃኒቶችን ሊመክሩ ይችላሉ፣ መዳኒቶቹም ለታካሚው በነፃ ሊቀርቡ ይገባል ምክያቱም ይህ የመድኃኒት በሚቋቋም የሳንባ ህመም (DR-TB) ህክምና አካል ነው።

ሰንጠረዥ 2 የተለመዱ መድኃኒት የሚቋቋም የሳንባ ህመም (DR-TB) ህክምና የጐንዮሽ ጉዳት ምልክቶችን፣ የሚከሰቱባቸውን ምክንያቶች እና ምልክቶቹን ለመቅረፍ ሊወሰዱ የሚገቡ እርምጃዎችን ያጠቃልላል።

**ሰንጠረዥ 2. መድኃኒት የሚቋቋም የሳንባ ህመም (DR-TB) የጐንዮሽ ጉዳቶች ምልክቶች፣ መንስኤዎችና እርምጃዎች**

| ምልክቶች | ምክያት ሊሆኑ የሚችሉ | ከህመሙ ምልክቶች ጋር ሊዛመዱ የሚችሉ **መድኃኒት የሚቋቋም የሳንባ ህመም (DR-TB)** መድኃኒቶች | ሊወሰዱ የሚችሉ እርምጃዎች |
|---|---|---|---|
| የማቅለሽለሽ/የማስታወክ ስሜት | የመድኃኒቶች መለወጥ፤የጉበት ችግር | Pretomanid, pyrazinamide, ማንኛውም የሳንባ ነቀርሳ መድኃኒት ሲጀመር | የደም ምርመራዎችን በማድረግ የጉበት ጤናን ይፈትሹ፣ ትኩረት ያልተሰጣቸውን መድኃኒቶች ላይ በማተኮር እና ማቅለሽለሽ ስሜትን የሚቀንሱ መዳኒቶችን መጠቀም፣ ጉበት ላይ ጉዳት ከተስተዋለ ጉበት እስኪያገግም ድረስ የቲቢ መድኃኒቶች ማቋረጥ |
| የቆዳ ቀለም/የዓይን ቀለም መቀየር | የቆዳ ቀለም መለወጥ፣ የጉበት ችግር | Clofazimine, pretomanid, pyrazinamide | የጉበትን ጉዳት በደም ምርመራዎች ይፈትሹ፣ ጉበት ላይ ጉዳት ከተስተዋለ የቲቢ መድኃኒቶች ጉበት እስኪያገግም ድረስ ሊቆሙ ይችላሉ። Clofazimine ከተቋረጠ በኋላ የቆዳ ቀለም መጨመር ቀስ በቀስ ይጠፋል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| የራስ ማዞር፣ እራስን መሳት፣ የደረት ሕመም | በልብ ውስጥ ባለው የኤሌክትሪክ ስርአት ላይ የሚከሰቱ ለውጦች | Bedaquiline, clofazimine, levofloxacin, moxifloxacin | ECG፣ የፖታስየም መጠን በደም ምርመራ ይፈትሹ። በልብ የኤሌክትሪክ ሥርዓት ላይ ለውጦች ከተስተዋሉ የቲቢ መድኃኒቶች ሊቋረጡ ይችላሉ። |
| የእይታ መቀየር | የዓይን ነርቭ ችግር | Linezolid | የዓይን ምርመራ፣ የዓይን ባለሙያ ማማከር፣ Linezolid መድኃኒት ማቋረጥ |
| የድካም ስሜት፣ የቆዳ ቀለም መቀየር፣ በቀላሉ የሚከሰት ቁስል ወይም መበለዝ | የደም ሴሎችን ከሚፈጥሩ የአጥንት ሕብረ ህዋሳት ጋር የተያያዙ ችግሮች | Linezolid | የደም ሴል ደረጃን በደም ምርመራዎች ይፈትሹ። ውጤቱ ጤናማ ካልሆነ የ Linezolid መጠን ሊቀነስ ወይም ሊቋረጥ ይችላል። |
| በእጅ ወይም በእግሮች ላይ የማቃጠል፣ የመደነዘዝ እና የሚወጋ ስሜት | የነርቭ ችግር | Linezolid | የእጆች እና እግሮች ነርቮች አካላዊ ምርመራ። ውጤቱ ያልተለመደ ከሆነ፣ የlinezolid መጠን ሊቀነስ ወይም ሊቆም ይችላል። |
| የመገጣጠሚያ/የጡንቻ ሕመም | የጡንቻዎች እና የመገጣጠሚያዎች መለስተኛ ህመም | Levofloxacin, moxifloxacin, pyrazinamide | የመገጣጠሚያዎች እና የጡንቻዎችን አካላዊ ምርመራ እና ህመሙን ሚቀንሱ  መድኃኒቶች መጠቀም። |
| ቅዠቶች፣ የአስተሳሰብ ለውጥ | መድኃኒቱ በአንጎል ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ | Delamanid | ራስን ወይም ሌሎችን የመጉዳት አደጋ አለመኖሩን ማረጋገጥ፣ ለእንቅልፍ የሚረዱ መድኃኒቶችን መጠቀም እና Delamanidን ማቋረጥ |

ህክምናው ከተጠናቀቀ በኋላም ክትትል መደረጉ መቀጠል አለበት። ይህ የሚደረገው የቲቢ በሽታ መመለሱን ወይም እንደገና መከሰቱን የሚያመለክቱ አዳዲስ ምልክቶችን ለመለየት ነው (ለምሳሌ አዲስ ሳል፣ አዲስ ትኩሳት፣ አዲስ የክብደት መቀነስ)። በተጨማሪም በሳንባ ነቀርሳ በሽታ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ የረጅም ጊዜ የጤና ጉዳዮችን ለመከታተል ይከናወናል። እነዚህ የጤና ችግሮች አንዳንድ ጊዜ “የሳንባ ህመም ተከታይ በሽታ” ተብለው ይጠራሉ። የመተንፈስ ችግር፣ የትንፋሽ እጥረት፣ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎችን የማከናወን ችግር፣ ወዘተ ሊያካትቱ ይችላሉ። በአንዳንድ የክምና ተቋማት ህክምናው ከተጠናቀቀ በኋላ የሚደረገው ክትትል በሳንባ ህመም ህክምናው ውስጥ ባልተሳተፈ የህክምና ባለሙያ ወይም በሳንባ ሐኪም የሚከናወን ይሆናል። ይሁን እንጂ የሳንባ ህክምና ላይ የተሰማሩ የጤና ባለሞያዎች ታክመው የዳኑ ሰዎችን ለመገምገም እና ተጨማሪ የሳንባ ነቀርሳ ምርመራዎችን ወይም ሌሎች አስፈላጊ ምርመራዎችን ወይም በሳንባ በሽታ  ሳቢያ  የተከሰቱትን  የመተንፈሻ አካላት በሽታ ወይም ሌሎች የጤና ችግሮችን ለመፍታት እርምጃዎችን በመውሰድ ለማገዝ ፈቃድ እና ችሎታው ሊኖራቸው ይገባል።

TAG

Treatment Action Group

www.treatmentactiongroup.org
90 Broad Street, Suite 2503 New York, NY 10004
Tel 212.253.7922, Fax 212.253.7923
tag@treatmentactiongroup.org